# ያገራችን ኑሮ

በገጠርም ያለህ ፣ እንዲሁም ከተማ
አዋጁን ተናገር ፣ የሰማህ ላልሰማ
የዛሬ ተረኞች ፣ አብይና ለማ
ላም ባልዋለችበት ፣ ለኩበት ለቀማ
ብሽሽቅ ነውና ፣ ለሱም ባይስማማ
አይጭኗት እንግዲህ ፣ ሆራንም በጋማ
ገንዳ ተበጀለት ፣ በታከለ ኡማ
አስፓልት አሳርሶ ፣ ይዝራበት ቄጠማ ።

የአይምሮ ድንክዬ ፣ ከስንዝር ያጠሩ
በድኩማን ስሌት ፣ አገር እየመሩ
ዘውዱ ተከርብቶ ፣ ዘውድ ሲሆን ጎፈሩ
ኢሬቻም ከሆራ ፣ ወጣ ከመንደሩ
እንደ ከብት ጭራ ፣ ከኋላ በቀሩ
በየስልጣኑ እርከን ፣ ድንጋይ እየዘሩ
ስርዓትና ወግ ፣ ገባ መቃብሩ ።

ዜጋም ተበላሽቶ ፣ ዘመን ተቀይሮ
ሴቷም ወንድ አትሻ ፣ እንዴት ተሞክሮ
ወንዱም ወንድ ሊዳር ፣ አየን ተሞሽሮ
የእርግማን ዘመን ፣ ግብር ያለ ተፈጥሮ
እንኳን ባህልና ፣ ያምላክ ቃል ተሽሮ
ይፈታተነናል ፣ ሰይጣንም አምርሮ ።

እንደኔ አጎንብሱ ፣ የሚለው ጎባጣ
እሱን ሸኘን ስንል ፣ መጣብን ቆማጣ
ከእሳት ወደ ረመጥ ፣ ይባስ እየመጣ
ይሉኝታ የሌለው ፣ ጭራሽ ዐይን ያወጣ
እንኳን የራስ ቅሉ ፣ አንጎሉም መላጣ
ዜጋን ከመበደል ፣ ከግፍ የማይወጣ
ሲያላምጥ በሚኖር ፣ የተበደልኩ ቋንጣ ።

ነገር እየከፋ ፣ ከአምናው ዘንድሮ
በዘመነ ኬኛ ፣ ሁሉም ተቀይሮ
በታኙ ሲፏልል ፣ አገሬ የሚል ታስሮ
የግርምቢጥ ዘመን ፣ በግ ሆና ቀበሮ
ህግና ስርዓት ፣ ቅጣምባሩ ዞሮ
ቅበላን በአሹቅ ፣ ፋሲካን በሽሮ
የባሰ አታምጣ ነው ፣ ያገራችን ኑሮ ።

ታዛቢው

September 22, 2019